# አዲስ የንጋት ጮራ ለብርሃን ልጆች

**በ ቦብ ጆንስ**
ጁላይ 2013



ለምንድን ነው የብርሃን ልጆች በዓመቱ አንዳንድ ጊዜያት ላይ በከፍተኛ ሰይጣናዊ ጥቃት በታች የሚሆኑት? በኤፌሶን 5 እኛ ብርሃን ነን ይላል።

*ቀድሞ ጨለማ ነበራችሁና፥ አሁን ግን በጌታ ብርሃን ናችሁ፤ እንደ ብርሃን ልጆች ተመላለሱ፤* ***(ኤፌሶን 5:8)***

ብርሃናቸው የበለጠ እየበራ ያሉ ሰዎች ከበፊቱ በላቀ ሁኔታ በጠንካራ ሰይጣናዊ ጥቃት ስር ሲሆኑ በቅርቡ አይቻለሁ። ስለዚህ ምን ማድረግ እንዳለብኝ እየጸለይሁ ሳለ፥ የሰማሁት ይህን ነው: “በምሽት ጥልቅ ጨለማ ላይ የብርሃን አምፖል ስታበራ፥ ምንድን ነው የሚስበው? ብዔል ዜቡል ይስባል!” ዝንቦች፣ የወባ ትንኞች እና ሌሎች ጎጂ ትኋኖች በትክክል የጠላትን አሰቃዮች ይወድዳሉ። የብርሃን ልጆችም የላቀ ሰይጣናዊ ጥቃት ሥር እየገቡ ናቸው። እነዚህ አሠቃዮች ሊያዘናጉና ብርሃናቸውን ሊያጠፉ ይመጣሉ።

በቅርቡ በጥቃት ሥር ከነበራችሁ በቀላሉ ያ ማለት ለእግዚአብሔር ብርቱ(ጠንካራ) ረሃብና ጥማት ስለነበራችሁ ብርሃናችሁ በርቶአል ማለት ነው። ስለዚህ ብርሃናችሁን አታጥፉት ወይንም አታውጡት። ምሽቱ ሲያልቅና የአዲስ ቀን የንጋት ጮራ ሲጀምር እነዚህ ነገሮች ሁሉ ያልፉሉና በዚያ ፈንታ የበለጠ ደምቆ እንዲበራ አድርጉ። በጣም በአጭር ጊዜ፥ ምናልባትም በጥቂት ሳምንታት ውስጥ፥ ምሽቱ ያልቃል አዲስ የብርሃን ቀንም እንደሚጀምር ይሰማኛል። እውነተኛ የእግዚአብሔርን ብርሃን ሊገልጥ ለብርሃን ልጆችም አዲስ አላማ ወደፊት እየመጣ ነው።

ስለዚህ እርሱ እየተናገረኝ ነው ብዬ የማምነው ይህን ነው። የእግዚአብሔር ልጆች እውነተኛ ብርሃን መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ምን እንደተጻፈ ይረዳል። ይህ ብዔል ዜቡል ግዛት(ስፍራ)፤ ዝንቦች፣ የወባ ትንኞች እና የጨለማ ነገሮች፥ ብርሃናችሁን ሊሰርቃችሁ ሲመጣ የበለጠ ይጨልማል። በዓለም ያለው ጨለማ የበለጠ ሲጨልም፥ የእግዚአብሔር ብርሃን የበለጠ ደምቆ ከእግዚአብሔር ልጆች

ይፈስሳል።

ይህ ጥቃት ለጥቂት-ጊዜ-የሚኖር ነገር ስለሆነና በአጭር ጊዜ ስለሚያልፍ ብዓል ዜቡል ብርሃናችሁን እንዲይዝ አትፍቀዱለት። ከዛ የቀን ብርሃን ይመጣል እና በእናንተ ውስጥ ያለው ብርሃን የሚገለጥበት ሰዓት እጅግ ቅርብ ነው። ስለዚህ አታፈግፍጉ ጠላትም ፍቅራችሁን፣ ደስታችሁን ወይም ሰላማችሁን እንዲሰርቅ አታድርጉ። ጠላት ዟሪ(short winded) ስለሆነና ጥቃቱም በአጭር ጊዜ ስለሚጠናቀቅ በዚህ የጥቃት ጊዜ እነርሱን(ፍቅራችሁን፣ ደስታችሁንና ሰላማችሁን) ያዟቸው። እናንተ ያላችሁ ብርሃንም **በወልድ**(**በልጁ በናዝሬቱ በጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ**) ብርሃን የበለጠ ደምቆ ይበራል።

## ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ትናንትና ዛሬ እስከ ለዘላለምም ያው ነው።

ስም የሌለው፥ የማይታወቅ፥ ጌታውና አምላኩ በሆነ በናዝሬቱ በኢየሱስ ክርስቶስ ጸንቶ የሚኖርና የሚታመን፥ ሊያደርግ የሚገባውን ያደረገ አንድ የማይጠቅም ባሪያ በመንፈስ ቅዱስ ተመርቶ ተረጎመው። ክብር ሁሉ፣ ኃይልም ብርታትና ጥበብም ውዳሴና ምስጋናም፣ ግርማና ሞገስም፣ ዝማሬና እልልታም ማዳንና ቅድስና ለቡሩክ መልካም ቅዱስ የእስራኤል አምላክ ለአባታችን ለእግዚአብሔር አብ ይሁን ለታረደው በጉም ለጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ለቡሩክ ቅዱስ መንፈሱም ብቻ ይሁን አሜን ሃሌ ሉያ። ማራናታ ጌታ ያሑሹዋ ሐማሺያክ የእግዚአብሔር ልጅ እግዚአብሔር ኢየሱስ ክርስቶስ ሆይ ቶሎ ና አሜን!

http://www.baptizingfire.com , http://fireofgodservants.blogspot.com/ , http://www.thelordshour.com , http://www.choothomas.org , http://www.Jesusministries.org/ , http://www.angeltv.org , http://www.Billygraham.org , http://free.messianicbible.com/ , http://www.levitt.tv/ , http://www.divinerevelations.info/amharic , http://www.heavenvisit.com , http://www.tribulation-now.org , http://www.voe.org/ , http://www.sidroth.org , http://repentandpreparetheway.org/ , http://www.shekinahworship.com/ , http://www.theblazingholyfire.com/ , http://www.thelastreformation.com , **http://www.bobjones.org/** , http://www.annarountree.com/ , http://www.beyondthephysicalrealm.com , http://www.shreveministries.org , http://www.blogtalkradio/tribulation-now , http://www.bullsere.kr/ http://www.blogtalkradio/thelordshour , http://www.blogtalkradio.com/discoveringthetruth , http://www.be4thefire.com/ , http://www.e-sword.net/ , http://lamarzulli.net/ , http://www.blogtalkradio.com/coming-apocalypse , http://www.irisglobal.org/ ,

http://www.morningstarministries.org/